# ከእኛ በኩል መልእክት ይሰማሉ!

ከማርች 2023 ጀምሮ ቨርጂኒያ የአባላትን የጤና ሽፋን መገምገም ትጀምራለች! Medicaid ወቅታዊ መረጃቸውን ሳይጠይቅ የአባላትን ሽፋን አይሰርዝም ወይም አይቀንስም፣ ከዚህም ሌላ የአባልነት መዝጋቶች ከኤፕሪል 30፣ 2023 በፊት አይከሰቱም።


በሽፋንዎ መቀጠልዎን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ደረጃዎች ይከተሉ:

## ይመርምሩ!

ስለ ቨርጂኒያ Medicaid የእድሳት ሂደት የተመለከተ መረጃ ይመልከቱ።

- ሁሉንም ኦፊሴላዊ መልዕክት፣ ኢሜይል ወይም ጽሁፎች በጥንቃቄ ያንብቡ
- ለወቅታዊ ኢሜይል እና ጽሁፍ ይመዝገቡ
- በማህበራዊ ትስስር ገጽ ላይ Cover Virginiaን ይከተሉ





## ምላሽ ይስጡ!

ከህክምና ድጋፍ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of Medical Assistance Services) (የቨርጂኒያ Medicaid)፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ Cover Virginia እና ቁጥጥር ከሚደረግበት የጤና እንክብካቤ እቅድዎ የሚከተሉትን የሚጠይቁ ኦፊሴላዊ ማስታወቂያዎች ሲደርሱዎ ምላሽ ይስጡ፡

- ወቅታዊ የግንኙነት መረጃ (የመልእክት አድራሻ፣ የኢሜይል አድራሻ እና ስልክ ቁጥሮች)
- የኦፊሴላዊ ማስታወቂያዎች ምላሽ



## ያድሱ!

የተጠየቀውን መረጃ እስከ ማብቂያ ቀን ድረስ በመላክ ሽፋንዎን ያድሱ።
ሁሉምንም ጥያቄዎች ይመልሱ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ከሚከተሉት መንገዶች መካከል በአንዱ አማካኝነት ማንኛውንም ለውጦች ያድርጉ:

- መዝገብዎን ከአካውንትዎ/መለያዎ ጋር ለማገናኘት የተሞሉትን ሰነዶች/ቅጾች በቅጽዎ ላይ የሚገኘውን የመዝገብ ቁጥር እና የመታወቂያ ቁጥር በመጠቀም በኦንላይን በ commonhelp.virginia.gov ያስገቡ።
- የእድሳት መረጃዎን ለማስገባት ለCover Virginia በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 ይደውሉ።
- የተሞላውን ቅጽ/ሰነዶች እስከ ማብቂያ ቀኑ ድረስ በቅጹ ወይም የማረጋገጫ ዝርዝሩ ላይ በተገለጸው አድራሻ በመልእክት ይላኩ።

DMAS Unwind II Post 0223 AM v2

### ቅጹን ወይም የማረጋገጫ ዝርዝሩን በተመለከተ ጥያቄዎች አሉዎት?

ለአካባቢዎ የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ወይም Cover Virginia ይደውሉ።
የሚጠየቀውን መረጃ ዝግጁ ያድርጉ።

እርዳታ ይፈልጋሉ?
ጥያቄዎች ካሉዎ ወይም የቋንቋ እገዛ አገልግሎቶች ወይም ትላልቅ ህትመት ከፈለጉ ለCover Virginia በስልክ ቁጥር 1-855- 242-8282 (TTY:1-888-221-1590) ይደውሉ፣ በ covervirginia@dmas.virginia.gov ኢሜይል ይላኩ፣ ወይም በ coverva.org. ይጎብኙን።

COVER VIRGINIA
Connecting Virginians to Affordable Health Insurance

ይህ ተቋም በፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ ላይ ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሄራዊ ማንነትን፣ ጾታን፣ ዕድሜን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት አድርጎ አያዳላም።

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM
DMAS